## «ሕዝብ ሲጉላላና ሥራ ሲበደል እኛ ለሥልጣን እንታደል!»

ከፀሐዬ ደባልቀው
ዋሽንግተን ዲሲ

አዋጅ ! አዋጅ ! ምታ ነጋሪት ክተት ሠራዊት ተብሎ አታሞ ተደልቆበታል:: በጥሩንባና በመለከት ታጅቦም እንዲህ ተለፍፍቦታል::

«የመንግሥት ሠራተኛ የሆንሽው በሥራሽ ላይ ለግሚ፣ በቀን ሠርተሽ የምትጨርሺውን ሥራ ሳምንት አቆይው....... ይላል ሰሞኑን የግንቦት 7 ንቅናቄ መሪ የሆኑት ዶ/ር ብርሃኑ ነጋ በአንደበታቸው የአዲስ ዓመት የትግል ጥሪ ባስተላለፉበት መልዕክት ላይ የተቀነጨበው ሐቲት! የዘመኑ ጉደኛ ጥሪ ቢባል የጉዳዩን ልኬት በሚገባ የሚገልጽ ይመስለኛል:: ግንቦት 7 ንቅናቄ ይህንን እኩይ ጦማሩን የአዲስ ዓመት የትግል ጥሪ ይለዋል:: »

ጥሪው የመንግሥት ሠራተኛ የሆነ ሁሉ የተሰጠውን ሕዝብን በአግባቡ የማገልገል ተግባሩን ገሸሽ እንዲያደርግ የሚማፀን ትእዛዝ አቀፍ ውትወታ ነው:: ይኸንን ሲያደርግ እንደ ዶ/ር ብርሃኑ ሙግት ወያኔ ይሽመደመዳል ባይ ናቸው:: እሳቸውንና መሰሎቻቸውን በዚህ የሽብርተኛና የቀውስ መንገድ ሥልጣን ኮርቻ ላይ ባቋራጭ እንዲፈናጠጡ እስካደረገ ድረስ ምን ገዷቸው ? ሀገር ለምኔ፣ ወገን ለምኔ ቢሉ እኩይ ዓላማቸውን ያሳካልኛል ብለው እስከገመቱ ድረስ የሕዝብ ጉዳይ ገደል ቢገባ ደንታቸውም አይደለም:: እንግዲያማ በመንግሥት በኩል የተዘረጋውን፣ የትምህርት፣ የጤና፣ የግብርና የውሃ፣ የመንገድ ፣ የስልክ የመብራት፣ የቤትና የሌሎችም መሠረታዊ አገልግሎት ሰጪ በሆኑ መ/ቤቶች የሚሠሩ ሠራተኞች ሥራችሁን በድሉ፣ አንተቱ

ማለት ሕዝብ ሊያገኝ የሚገባውን ግልጋሎት በወቅቱ አትስጡ ከማለት ውጭ ከቶ ሌላ ትርጉም ሊሰጠው ይችላልን? ሕዝብ ሊያገኝ የሚገባውን ግልጋሎት ንፈጉ ማለት ትምህርት የራበውን፣ በሽታ የሚያንገበግበውን፣ መንገኛ የሚያስፈልገውን፣ ውሃ የጠማውን፣ የእርሻ ግብአት የሚሻውንና በገበያ መረጃ እጦት የሚደናበረውን፣ ፍትህ እሚማለደውን ዜጋ ሁሉ በጨለማ ይዳክር፣ በስቃይና በቀጣና ይገረፍ በማለት ፍርደ ገምድላዊ ብይን መስጠት አይለምን?

ዳሩ የግንቦት 7 ንቅናቄ መሪዎች ትላንትናም በጀብደኝነት የእሪታና ኡኡታ ቡድን፣ የጩኸትና የሁካታ ግብረ ኃይል እያሉ ወጣቱን የጥይት ራት ሲያደርጉት በሰላማዊ ትግል የአደባባይ ሁከትና ነውጥ በመቀስቀስ እሱን ከፊት አስቀድመው የእሳት ራት ሲሆን የለንበትም ብለው ከወላፈኑ መሸሻቸው ያደባባይ ሚስጥር መሆኑ ያጤኗል::

እረ የኢትዮጵያ ሕዝብ እስከ መቼ ድረስ ነው የነውጠኞች የአሸባሪዎች የሥርዓተ አልበኞችና የጅብደኞች፣ የሥልጣን መወጣጫ አሸንዳ ቤተ ሙከራ የሚሆነው እረ እስከ መቼ ድረስ ነው በሥሙ የሚነገደው ?

ለጊዜ ምስጋና ይግባውና ወቅት ባለበት የማይቆም ምን ጊዜም ታዳሽ በመሆኑ ሕዝቡ ዛሬ በሀገሪቱ በ18 ዓመታት ውስጥ 31 የመንግሥት ዩኒቨርስቲዎችን በዓይኑ በብረቱ እያየ፣ ትላንት ሁለት ብቻ እንደነበሩ ማስታወስ አይችልም ለማለት አንዳንድ ፖለቲከኞች ሲቃጣቸው ሲሰማ በቃ ሊላቸው ይገባል::

በ1983 የደርግ ውድቀት ማግስት በመላ ሀገሪቱ ሁለት ነጥብ ስምንት ብቻ የነበረው የተማሪ ቁጥር በዛሬይቱ ኢትዮጵያ ከሰማንያ ሚሊዮን ሕዝብ መካከል ከመዋዕለ ሕፃናት እስከ ከፍተኛው የዩኒቨርስቲ ትምህርት ደረጃ ከአሥራ አራት ሚሊዮን ያላነሱ ተማሪዎች በየዕለቱ በየትምህርት ቤቱ ሲርመሰመሱ እያስተዋለ እሱ በተዋናይነትና በታሪክ ሠሪነት እየዋጀ የገነባውን የሥርዓቱን ማበብ ዓይኔን ግንባር ያርገው ብለው ሲሸመጥጡ ሲያይ አይ አሁንስ በዛ ሊላቸው ይገባል::

ከአሥራ ስምንት ዓመታት በፊት በሀገራችን ሦስት የመንግሥት ባንኮች የነበሩበት ዛሬ አሥራ አንድ የግል ባንኮችን ጨምሮ ወደ 14 ባንኮች ደርሰዋል:: ዛሬ በሀገራችን አሥር ሺህ የገጠር ቀበሌዎች የስልክ አገልግሎት እንዲያገኙ ተደርጓል:: የመደበኛው የቤት ስልክ አገልግሎት ቁጥር ግማሽ ሚሊዮን ያህል ሆኗል:: የሞባይል ስልክ አገልግሎትንም ስናይ በአሁኑ ጊዜ ወደ ሁለት ሚሊዮን ደንበኞችን አዳርሷል::

541 ወረዳዎች የወረዳኔት 642 ሁለተኛ ደጃ ት/ቤቶች የስኩልኔት እና እንዲሁም 29 የግብርና የምርምር ተቋማት የአግሪኔት የኢንተርኔት አገልግሎት መረብ ተሳስረዋል።

እንግዲህ የግንቦት 7 ንቅናቄ መሪ የአዲስ ዓመት የትግል ጥሪ እነኝህ አገልግሎቶች ይሰናከሉ፣ ሕዝቡ ተገቢው አገልግሎት ተነፍጎት ይጉላላ፣ እናም በመጨረሻ ሕዝቡ ሲያማርር በሚፈጥረው ክፍተት እኛ የአዞ እንባ እያነባን ሙሾ እየወረድን አለንልህ ብለን የምንቋምጥለትን በትረ ሥልጣን እንጨብጣለን የሚል ስሌት ሕዝቡን ከመናቅና ከአማራጭ የፖሊሲ ሰነድ አቅርቦት ድህነትና የፖለቲካ ኘሮግራም እጦት የሚመነጭ ባወጣ ያውጣው ግልብ የጥላቻና የግብዝነት አቋም የወለደው የትግል ስልት መሆኑን የኢትዮጵያ ሕዝብ ዕለት በዕለት እየፈካና እየጐመራ፣ በሚሄደውና በውጤቱና በፍሬው ተጨባጭ ለውጥ እያየበትና ጥቅሙንም እያጣጣመበት በመሄድ ላይ ያለውን ዲሞክራሲያዊና ፍትሀዊ ለውጥ ለድርድር አያቀርብም እላለሁ ሠላም !